

# ያለ የቤት ውስጥ ሰራተኞች የእንክብካቤ ኢኮኖሚ ሊኖር አይችልም! ማኒፌስቷችን/ መግለጫችን

awid



# እኛ የፌሚኒስት እና የሰራተኞች ንቅናቄ አራማጆች አንድ ላይ በመሆን የጋራ ራዕያችን የሆነውን የቤት ውስጥ ሰራተኞችን መብት ያማከለ የእንክብካቤ ኢኮኖሚ ላይ ዝርዝር አቋማችንን አስፍረናል፡

1

የቤት ውስጥ ሰራተኞችን ድምፅ ፣ መብት እና አመራር ያላማከለ እና የቤት ውስጥ ሰራተኞችን እንደመሳሪያ ብቻ በመጠቀም የእንክብካቤ ኢኮኖሚን ለማጎልበት የተዘረጋ ስርዓትን እንቃወማለን። **ቀዳሚው ትግል የሰው ልጆችን ክብር ለማስጠበቅ የሚደረግ መሆን አለበት።** ትንሽ የሚባል እና ንፁህ ያልሆነ ስራ የለም። ተገዢዎች ሳንሆን ሰራተኞች ነን፤ ከሁሉም በላይ መብት ያለን የሰው ልጆች ነን።

2

**እንክብካቤ የጋራ ሃላፊነት እንጂ በተወሰኑ ሰዎች ጫንቃ ላይ የሚወድቅ ስራ ያልሆነበት** ነገን እንመኛለን። የሁሉም ሰራተኞች ነፃነት የተሳሰረ ነው። የእንክብከቤ ስራ ስደተኛ፣ ጥቁር እና ከማህበረሰብ በተገለሉ ሴቶች ላይ ብቻ የሚወድቅ ሸክም መሆኑ ቀርቶ፣ ሁሉም ሰው በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀጠናዎች ላይ እኩል እንዲሳተፍ የሚያስችል የሥራ ክፍፍልን የሚደግፉ መዋቅሮች እንዲፈጠሩ እንጠይቀለን።

3

**ዘርን እና መደብን ያማከለ መድሎዓዊ አስተሳሰብን የሚቃረን ባህል** በማንኛውም ክልል እና የማህበረሰብ አኗኗር ውስጥ የሚደረግ **የቤት ውስጥ ሰራተኞች የነፃነት ትግል ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ** ተደርጎ እንዲታሰብ እንመኛለን።

በቤት ውስጥም ሆነ ውጪ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ፣ ለግል አሰሪዎችም ሆነ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ **ህይወትን ለማስቀጠል የሚያስፈልግ ማንኛውም ስራ የእንክብካቤ ስራ እንደሆነ የሚረዳ አቋምን ይዘናል።**

4

5

**የአባወራ ስርዓት የክህሎት እና እሴት ተዋረድ** "በምርት" ኢኮኖሚው ውስጥ ለእንክብካቤ ስራ እና ለሌሎች ስራዎች የሚሰጠውን የተለያየ እርከን **ማፍረስ እንሻለን።** የመኖሪያ ስፍራ መሰረታዊ ከሆኑ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ነፃነት እና መብት ጥያቄዎች የተገለለ የግል ስፍራ ነው የሚል ፅንሰ-ሃሳብን እንቃወማለን።

የቤት ውስጥ ሰራተኞች፤ የፆታ፣ **የስነ-ተዋልዶ እና ደህንነት፤** እንዲሁም **የእራስ አካልን በራስ የማስተዳደር ነፃነታቸውን** መተግበር ችለው እና ከስነ-ተዋልዶ ፣ ከጥቃት እና መገደድ እንዲሁም ከአድሎዓዊ አሰራር ነፃ ከመሆን ጋር የተገናኙ ጉዳዮች ላይ በነፃነት እና በሙሉ እውቀት ለራሳቸው የመወሰን ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል።

6

# 7

የቤት ሰራተኞችም ጭምር የእንክብካቤ ተቀባዮች መሆናቸውን ተረድተን፤ ተደራራቢ የሆነ ጫናን ለማስቀረት፤ ለህፃናት የሚሰጥ እንክብካቤን ጨምሮ ሌሎች **የህዝብ የእንክብካቤ አገልግሎቶችን አቅርቦት** ሊያገኙ ይገባል።

# 8

የእንክብካቤ ስራ የሚገባውን እውቅና ማግኘት፣ መካስ እና በማህበረሰብ መሃል በጋራ መከፋፈል እንዳለበት እንዲሁም **እንክብካቤ ሰብዓዊ መብት እና ለህዝብ ፍጆታ የሚውል ጥቅም** እንደሆነ አጥብቀን እናምናለን።

# 9

በመካከለኛው ምስራቅ አለም ላይ እንዳለው **እንደ ካፋላ ስርዓት** አይነት በስደተኛ ሰራተኞች ላይ የሚፈፀም አስገዳጅ የጉልበት ብዝበዛን የሚያበረታቱ የጭቆና ስርዓቶችን አንድ ላይ **እንዋጋለን።** ይህም መቆም እንዳለበት እናምናለን። ሁላችንም ነፃ የሆነ ሕይወት ይገባናል።

# 10

ክብርን የጠበቀ ስራ ምን እንደሚመስል ከሚያስርዳ እንደ የአለም አቀፍ የሰራተኞች ድርጅት (ኣይ. ኤል. ኦ) መዋቅር እና ሌሎች ወረቀት ላይ ከሰፈሩ ህጋዊ ከለላዎች በዘለለ የአሰሪዎች፣ የመንግስታት እና ብሎም አጠቃላይ **ማህበረሰባዊ የሆኑ የባህል እና አስተሳሰብ ለውጦችን** የማጎልበት ስራ ይጠበቅብናል።



**የቤት ውስጥ ሰራተኞች መብት፣ ውክልና እና የቤት ውስጥ ሰራተኞች የንቅናቄ አመራርን ያማከለ የእንክብካቤ እኮኖሚ ለማስፈን የምናደርገው ጥረት ላይ ሌሎች የፌሚኒስት እና ማህበራዊ ንቅናቄዎች እንዲቀላቀሉን ጥሪያችንን እናደርሳለን።**



# መግለጫችን ውስብስብ ለሆነው ነባራዊ ሁኔታ መልስ የሚሰጥ ነው

የቤት ውስጥ ሰራተኞች እና የእንክብካቤ ስራ ከኮቪድ 19 አለም አቀፋዊ ወረርሺኝ በኋላ ብዙ አትኩሮትን እያገኘ ነው። ይህም የሆነው ተደራራቢ ከነበረው አለም አቀፍ ቀውስ አለምን በአጠቃላይ ተሸክሞ ማሳለፍ የቻለው እና ትልቅ ሚና የተጫወተው ይህ የቤት ውስጥ እና የእንክብካቤ ስራ በመሆኑ ነው። የአለም ባንክ፣ የአለም አቀፍ ተቋምን (ኣይ. ኤም. ኤፍ)፤ እንዲሁም ሌሎች የባለብዙ ትስስር ድርጅቶች የእንክብካቤ እና የቤት ውስጥ ስራ የአለምን ኢኮኖሚ ለማስጠበቅ ላበረከተው ሚና እውቅና ይሰጣሉ ። ነገር ግን፤ ይህ እውቅና እንክብካቤን እንደ ሰብዓዊ መብት እና የህዝብ ጥቅም እንደሆነ እንዲሁም ፤ በዚህ ዘርፍ ተሰማርተው የሚገኙ ሰራተኞችን መብት የሚያማክል እና የሚረዳ በመሆን ፋንታ፣ ጥቅማዊ አሰራርን የተከተለ (የእንክብካቤ ስራ “የምርት” ኢኮኖሚን ያስጠብቃል) እና ከእንክብካቤ ስራ በሚገኝ አገልግሎት ለመበልፀግ የተዘጋጀ እውቅና ነው የሚል ትንታኔ ይዘናል።

የቤት ውስጥ ሰራተኞች ጉልበት አሁንም የሚገባውን ዋጋ/እሴት እንዲሁም እውቅና ሳያገኝ እና አትኩሮት ሳይሰጠው ቀጥሏል። ይህም የሆነው የቤት ውስጥ ስራ በደሃ እና መብታቸው ባልተጠበቀላቸው ሴቶች ብቻ የሚሰራ ስራ ተደርጎ ስለሚታይ ነው። በተለይ ደግሞ የአየር ንብረት እና የምጣኔ ሃብት ችግሮች በተፋፋሙበት እና ዋጋ በናረበት፣ እንዲሁም የሰራተኞች ደሞዝ በላሸቀበት በአሁኑ ጊዜ፤ የቤት ውስጥ ሰራተኞች በዝባዥ የሆነ ክፍያን እና የስራ ሁኔታን ከከፍተኛ የእንክብካቤ ጫና ጋር ለመቀበል ተገደው ይገኛሉ።

በአጭሩ የቤት ውስጥ ስራ የሚናቀው የሴትነት ባህሪ ስለተሰጠው ነው። የእንክብካቤ ኢኮኖሚው አሁንም ድረስ ዘርን፣ ቀኝ ገዢነትን እና መደብን ባተኮረ ታሪክ የተቀረፀ ነው። ባለፈው ታሪክ ውስጥ ዛሬንም ጨምሮ የእንክብካቤ ጫና አለአግባብ የሚወድቀው ድሃ፣ ስደተኛ እና በመደባቸው በተበደሉ ሴቶች ላይ ነው። የዘር፣ የእርከን፣ የመደብ እና የስርዓተ-ፆታ ማንነቶች ተደራራቢት ለኢ-እኩልነት መነሻ ሆነው ሳለ፤ በተለያዩ ፖሊሲዎች እና የህግ ማዕቀፎች ለሌላ ስራ ዘርፎች እውቅና ሲሰጥ እና ቁጥጥር ሲደረግ እነዚህ ተደራራቢ ጭቆናዎች ግን ጭራሹኑ ተረስተዋል።

**የተወሰኑ ሀገራቶች ላይ በመደብ የተጨቆኑ የቤት ውስጥ ሰራተኞች የባርነት አገዛዝ ቀጥሏል። የእነዚህ ሰራተኞች ሰውነት ንፅህና የጎደለው እንደሆነ ከሚያስተምረው የብራህማኒካል አስተሳሰብ ጋር የተገናኘ ነው። ከፍተኛ የመደብ አሰሪዎች ዝቅተኛ መደብ ላይ የሚገኙ ሴቶችን አነስተኛ ገንዘብ ተከፋይ የሆኑ የፅዳት ስራዎችን ብቻ እንዲሰሩ ይገድቧቸዋል። ይህንንም የሚያደርጉት ክብራቸውን ባልጠበቀ እና ለጥቃት በሚዳርጋቸው ሁኔታ እያሰሯቸው ነው።**

የተደራጁ ጥቁር የቤት ውስጥ ሰራተኞች ከረጅም ጊዜ አንስቶ የሰራተኞች መብት እና የጥቁር ሰዎች የነፃነት ንቅናቄዎች ውስጥ ሲሳተፉ ቆይተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ በላቲን አሜሪካ እንደ ብራዚል እና ኮሎምቢያ ባሉ ሃገራቶች ውስጥ የሰራተኞች ማህበራት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው እና አሁን ላይ እየተተገበረ ያለውን መዋቅራዊ ዘረኝነት በቀረፀው የባርነት ትውፊት እየተጎዱ ይገኛሉ፡፡ ብዙሃኑ ከ 5 እስከ 7 አመታቸው ጀምሮ በአስገዳጅ ስደት ተጠቂ ሆነው በነጮች ቤት ውስጥ ያለምንም ክፍያ፣ ምግብ እና ልብስ ብቻ ቃል እየተገባላቸው እና እውን የማይሆን የተሻለ የወደፊት ኑሮን እየጠበቁ ሲሰሩ የቆዩበትን የህይወት ታሪክ ተሸክመዋል። እነዚህ ታሪኮች በዘር በሚከፋፍሉ ፖሊሲ እና ህጎች ምክንያት የነጭ ቤተሰቦች ቤት ውስጥ ከነልጆቻቸው የታገቱ እና ከትውልድ ትውልድ የተላለፈ ድህነት ተጠቂ እንዲሆኑ የተደረጉ የደቡብ አፍሪካ ጥቁር ሴቶች ጭምር የሚጋሩዋቸው ታሪኮች ናቸው፡፡ ዘረኝነትን የመቃወም ትግል ከቤት ውስጥ ሰራተኞች የነፃነት ትግል እና ክብርን የጠበቀ ስራን የመስራት መብታቸውን ከማስጠበቅ ትግል ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው።

ሰራተኞች የተሻለ የኑሮ ሁኔታ ፍለጋ እና ቤተሰቦቻቸውን እና ማህበረሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩበትን መንገድ ፍለጋ ይሰደዳሉ፤ ብዙውን ጊዜ ከጭንቀት፣ ጥቃት እና የአየር ንብረት መዛባት ጋር ከሚመጡ ጎጂ ሁኔታዎች ለማምለጥም ጭምር ይሸሻሉ። እነዚህ ስደተኛ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ለተነሱበትም ለተሰደዱበትም ሀገራት ኢኮኖሚ አስተዋፅዖ ያደርጋሉ፤ ነገር ግን እንደ ዝቅተኛ ሰራተኛ እና እንደ ማይፈለግ ስደተኛ ይታያሉ። ወደ መሃከለኛው ምስራቅ አለም የተሰደዱ አፍሪካዊ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ሴቶች የኑሮ እውነታዎች፤ ሰራተኞችን ከአሰሪዎቻቸው ጋር ያለምንም የምርጫ ነፃነት እና እንቅስቃሴ የሚሰሩ ስርዓቶች ማሳያ ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ስደተኛ በመሆናቸው ምክንያት ለሚያጋጥሟቸው የጥቃት ተጋላጭነትን በመጠቀም ለባሰ ብዝበዛ እና ለወሲባዊ እንዲሁም ሌሎች ፆታዊ ጥቃቶች ተጋላጭ ያረጓቸዋል። አብዛኛውን ጊዜ፤ ላኪ እና ተቀባይ መንግስታት፤ አለምአቀፍ ድርጅቶች እና አሰሪዎች የቤት ውስጥ ሰራተኞችን እንደ ክህሎት አልባ፣ ተመጣጣኝ ክፍያ እና ክብር እንዲሁም መሰረታዊ ሰብዓዊ መብት እንደማይገባቸው ሰራተኞች ይቆጥሩዋቸዋል።



# እኛ እነዚህን ሰብዓዊነት የጎደላቸው አስተሳሰቦችን እንቃወማለን።

የፌሚኒስት ኢኮኖሚን ለመገንባት አሁን ላይ ያለውን አሰራር መስበር ይጠይቃል። በእንክብካቤ ኢኮኖሚ ውስጥ ያሉ የሰራተኛ መብቶችን ለማስጠበቅ የሚሰራው ትግላችን፤ ኢ-እኩልነት እና የጉልበት እንዲሁም የአለም ሃብት ብዝበዛን ከሚያበረታቱ የአባወራ ስርዓት እና ካፒታሊስት መዋቅር ተቃርኖ ከሚሰራው ሰፊ ትግል ጋር ተለያይቶ የሚታይ አይደለም።

በአለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የሚደገፉ እና የሚበረታቱ ኒዮ-ሊበራል ፖሊሲዎች የመንግስትን የመንከባከብ ግዴታን አፍርሰውታል። ክብሩ የተጠበቀ ህይወትን ለመኖር የሚያስችሉ መሰረተ ልማቶችን ጨምሮ፤ ለማህበረሰብ ደህንነት፣ ለህዝብ ጤንነት፣ ለምግብ ዋስትና እና አነስተኛ ገቢ ላላቸው የሚሆኑ መኖሪያዎች ይሰጡ የነበሩ የገንዘብ ድጋፎች እጅጉን ተመናምነዋል፡፡ ለህዝብ አስፈላጊ የሆኑ የማህበረሰብ መሰረተ ልማቶች መፈራረስ ጀርባ ያለው እና በግልፅ ግን የማይነገረው አስተሳሰብ ፤ እነዚህ ሁሉ ክፍተቶች በሴቶች ጉልበት መሞላት ይችላሉ የሚለው እምነት ነው።

በካፒታሊስት አለገደብ ብዝበዛ የተፈጠረው ቀውስ አሁን ፍሬ አፍርቶ በአየር ንብረት መዛባት የህብረተሰቡ መተዳደሪያዎችን እያጠፋ ይገኛል፡፡ የቤት ውስጥ ሰራተኞች ደሞ ያለአግባብ በዚ ቀውስ ከሌለው በተለይ ይጠቃሉ። ይህ ደግሞ በተለየ ሁኔታ መሬት ለማዕድን ስራዎች አድሎ በማድረግ በመሰጠቱ የቀረ መሬት በማይኖርበት ጊዜ እና በሌላ በኩል ደግሞ መሬትን ከማግኘት ጋር የተመረኮዘ የእርሻ እና የምግብ ዋስትና ህይወትን ለማስቀጠል አስፈላጊ በሚሆንብት ጊዜ ጎልቶ ይታያል። የንፁህ ውሃ፣ እንጨት እና ሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች መመናመን በሚታይባቸው የገጠር አካባቢዎች ላይ ደግሞ እነዚህን ፈልጎ እና ሰብስቦ ለቤተሰብ የማዋል ስራ የተጣለባቸው ሴቶች ላይ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡ በከተማ ቦታዎች ላይ፤ በቂ መኖሪያ የሌላቸው ሰራተኞች ለሙቀት ወበቅ እና ሌሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ይጋፈጣሉ። ይህ ደግሞ ያለምንም ማህበራዊ ጥበቃ ለሚሰሩ ሴቶች የበለጠ የእንክብካቤ ጫና ይፍጥርባቸዋል።

አይ. ኤል. ኦ የ5R መዋቅርን ከማካተቱ በፊት የቤት ውስጥ እና የእንክብካቤ ሰራተኞች ንቅናቄዎች በእንክብካቤ አጀንዳ ላይ ሲሰሩ ቆይተዋል። ይህ መግለጫ በእነዚህ ንቅናቄዎች በተነሱ ጥያቄዎች ላይ የሚገነባ ሲሆን፤ ለምሳሌ እንደ የአይ.ዲ.ደብሊዩ.ኤፍ አባላት ለአካታች የእንክብካቤ አጀንዳ፣ 6ተኛ R ጨምሮ የእንክብካቤ መዋቅር ኢኮኖሚው ተንከባካቢ ኢኮኖሚ እንዲሆን በተለየ መልኩ መገንባት እንዳለበት (reframe) ያሳሰበው የኢኤስሲአር-ኔት ሶሻል ፓክት ኦን ኬር እንዲሁም የፐብሊክ ሰርቪስስ እንተርናሽናል በእንክብካቤ ዙሪያ የህብረተሰብን አደረጃጀት እንደገና የመገንባት መግለጫን ያካትታል። እነዚህ የተጠቀሱት ምሳሌዎች በእንክብካቤ እና የቤት ሰራተኞች መብቶች ዙሪያ የሚጠቀሱ ከዓለምአቀፍ፣ ከተለያዩ ክልሎች እና የማህበረሰብ የጋራ ተነሳሽነቶች መሃል ናቸው።

ለኢኮኖሚያችን
ያለን የፌሚኒስት
አተያይ/አቀራረብ
እንክብካቤን በተለየ
መልኩ ማሰብ
የሚችል ስር ነቀል
ስርዓትን ይፈልጋል።

ለሴቶች የዕድገት መብት የተቋቋመው ማህበር (ኤ.ደብልዩ.አይ.ዲ) አለም አቀፍ፥ ፌሚኒስት ፥ አባልነት እና ንቅናቄን የሚደግፍ ድርጅት ነው።
www.awid.org

ይህ መግለጫ እውን እንዲሆን በጋራ ያበረከቱ የቤት ውስጥ ሰራተኞች፥ የተለያዩ ጥምረቶች እና ኔትወርኮች፥ እንዲሁም የሰራተኛ እና ፌሚኒስት ንቅናቄዎችን እውቅና መስጠት እና ማመስገን እንፈልጋለን። እነዚህም እነ ፊሽ አይፒ፥ ናንሲ ካቺንግዌ፥ አርያን ኪቶኮ፥ ብራሃም ፕረስ፥ ማርያም አል ቲቢ፥ ምደሃ ትሃቴ፥ ፋርሃና አፍሪን ቲህቲ፥ ሮውላ ሰግሃይር፥ ማሪያና ጎሜሴሪያ፥ ቻርሊን ሜይ፥ ፍራሲስካ አንክራ፥ ዋንግ ሜንግ፥ ባንዳና ፓታኒክ፥ አድሪያና ፓዝ፥ አሌሃንድራ ስካምፒኒ፥ ኢዳ ሌ ብላንክ፥ ማሪያ ቦቴሮ፥ ኬንሳኒ ሞቲሌኒ፥ ጁሊያ ሶዓኒሪና፥ ኢኒ ሌስታሪ፥ ጁዓና ቶሌዳ፥ ኢውጂና ሊካር፥ ክላውዲያ ላዛሮ፥ ቤቲ ቪሊሲያ ሚትማ፥ ባስማ ኢድ፥ ክላሪቤድ ፓላሲዮስ ጋርሲያ፥ ሞና ኢዛት፥ ኢሲ ኮቶር፥ ሜሪ አን አቡንዳ፥ እና ኬሪን ሜትዝ አቡ ህሜድን ያጠቃልላል።

ክርኤቲቭ ኮመንስ አትሪቢውሽን ነን ኮሜርሻል ሼርአላይክ 4.0 እንተርናሽናል (ሲሲ ቢዋይ-ኤንሲ-ኤስኤ 4.0)
www.creativecommons.org

AWID (2023)